# ታላቅ የኢትዮጵያውያን የተቃውሞ ሰልፍ ጥሪ

## በብራሰልስ-ቤልጂየም



### በአውሮፓ የቅንጂትና የህብረት ድጋፍ ኮሚቴዎች በጋራ <u>የተዘጋጀ</u>

በአገራችን በቅርቡ በተካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ ህዝባችን በምርጫ ካርድ ቅንጂትንና ህብረት
ን በመምረጥ ገዥውን የወያኔ /ኢህአዴግ አገዛዝ  ለመጣል የወሰደውን እርምጃ በመቀልበስ የም
ርጫ ቦርድ ወያኔ/ኢህአዴግን አሸናፊ አድርጓል፡፡ ይህንን የማጭበርብር ውጤት የአውሮፓ ህብረ
ት ታዛቢዎች ያጋለጡት ከመሆኑም በላይ የአሜሪካ መንግስትም የህዝብ ድምጽ መጭበርበር እን
ደሌለበት እጥብቃ እያሳሰበች ነው፡፡ ዛሬ ወያኔ /ኢህአዴግና ተለጣፊው የምርጫ ቦርድ በአደባባይ
የህዝብ ድምጽ ተሰርቆ የመለሰ ዜናዊ አገዛዝ ለተጨማሪ አምስት አመታት በህዝባችን ትከሻ ላይ
እንዲያሰራፋ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ህዝባችን በድምጹ ያስወገደውን የወያኔ /ኢህአዴግ ዘረኛ
አገዛዝ ህዝብን እያፈነና እየገደለ አሸናፊ ተቃዋሚ ሃይሎችን እያሳደደ በጠብመንጃ አፈሙዝ  የ
ስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ማንኛቸውንም የሃይል እርምጃ እየወሰደ ይገኛል፡፡ የተዘረፈው የህዝባ
ችን ድምጽ እንዲከበር፥ በወያኔ/ኢህአዴግ የአፈናና የጸጥታ ሃይሎች  በህዝባችንና በተቃዋሚ ሃየ
ሎች አባሎችና ደጋፊዎች ላይ እየተወሰደ ያለው ወከባ ፥እስራትና ግድያ በአስቸኳይ እንዲቆም፥
የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች የወሰዱትን አቋም እያደነቅን የአውሮፓ መንግስታትም
ይህንን የተጭበረበረ የምርጫ ውጤትና የሚቋቋመውን የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት እንዳይቀበሉ
ትና  ድምጹን ከተነጠቀው የኢትዮፕያ ህዝብ ጎን እንዲቆም ለማሳሰብና አለም አቀፉም ህብረተ
ሰብ ለዚህ አምባገነን ሃይል የሚሰጡትን ድጋፍ አቁሞ ትርጉም ያለው ተጽእኖ በመለሰ አገዛዝ ላ
ይ በማድረግ ከኢትዮጵያ ህዝብና ተቃዋሚ ዴሞክራቲክ ሃይሎች ጎን በመቆም ለነጻነትና ለዴሞክ
ራሲ የሚደረገውን ትግል እንዲደግፍ ለመጠየቅ ነው፡፡
በአውሮፓ የቅንጅትና የህብረት ድጋፍ ኮሚቴዎች በጋራ በጠሩት በዚህ ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ
ላይ በመለሰ አገዛዝ የተቀማውን የህዝባችንን  ድምጽ ለማስከበርና ህዝባችን የሚያካሂደውን ተጋ
ድሎ ለማገዝ እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንነሳና በሰልፉ በንቃት እንድንሳተፍ አገራዊ ጥሪ
እናቀርባለን! የሰልፉ ቀንና ቦታ  September 22, 2005 ከጧቱ 10:00
ሰአት ጀምሮ በብራሰልስ ከተማ Metro Shuman በሚባለው በአውሮፓ ፓርላማ ፊት ለፊት
በሚገኘው ቦታ ነው፡፡ ከሰልፉም በቃላ ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ የተዘጋጀ መሆኑን ጨምረን
እንገልጻለን፡፡ የተባበረ ህዝብ ምን ጊዜም አሸናፊ ነው ! Der Bus startet am Mittwoch am Haupt Bahnof in
Frankfurt am Main am Mittwoch um 24 Uhr !

<u>ማሳሰቢያ</u>

ወደ ሰልፉ ለመሄድ በትላልቅ ከተሞች በቀላል ዋጋ አውቶቡሶች የተዘጋጁ ስለሆነ በሚቀጥሉት ስልኮች በመደወ
ል መመዝገብ ይቻላል፡፡ አስቀድሞ ያልተመዘገበ ለጉዞው ችግር ሊገጥመው ይችላል፡፡
ለመመዝገብ በሚከተሉት የስልክ ቁጥሮች ይጠቀሙ፡፡

**Tel**. 0162 690 3682 , 0621 1060 27,  0176 244 66416, 0172 4621849

ሰልፉ በምንም መንገድ የማይቀየር መሆኑን አጥብቀን እናሳስባለን፦ **www.ethiogermany.de**